በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? …

ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትና የይሆዋ ምስክሮች

ክፍል ሰባት

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

በሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
መጋቢት ፲፮ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

1. ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች (The 7th Day Adventists)

- እነዚህ ከመጥምቃውያን (Baptist) ጋር የሚመሳሰሉና ለብሉይ ኪዳን ታላቅ ሥፍራ አለን የሚሉ በአሜሪካ የተፈጠሩ መናፍቃን ናቸው።

- ከ1830 እስከ 1840 ዓ.ም. አካባቢ በዊሊያም ሚለር አማካይነት ተቋቋመ።

- ዊሊያም ሚለር መጽሐፍ ቅዱስን ካነበበ በኋላ ምጽአት ተቃርቧል፤ የክርስቶስ መንግሥት ለ1000 ዓመት በዓለም የሚሆንበት ጊዜ ደርሷል አለ።

- #ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን
 የሚያውቅ የለም።; ማቴ 24፡36 ላይ የተጻፈውን በአግባብ ስላልተረዳ ይህ ጊዜ ቀንና ሰዓትን እንጂ ዓመታትን አይመለከትም ወደሚል ድምዳሜ ደረሰ።

- በራሱም ዘዴ ጊዘውን በማስላት ወይም በመቀመር የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በ1844 ዓ.ም. ነው ብሎ አወጀ። ሰዓቱንና ጊዜውን ቦታውንም ጨምሮ ኦክቶበር 22፣ 1844 ዓ.ም. በማለት ክርስቶስም የሚመጣበት ተራራ በኒውዮርክ ግዛት የሚገኝ መሆኑንም ገለጸ።

1. ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች (The 7th Day Adventists)…

-ተከታዮቹም ነጭ ልብስ ለብሰው በፍርድ ተራራ በብዙ ቁጥር ተሰበሰቡ፡፡ ቀኑ እንደተባለው ሳይሆን ቢያልፍም ሕዝቡ ግን ተከትለውታል፡፡ ይህንን አጋጣሚም ክርስቲያኖች ያልሆኑት ሁሉ የተከታዮቻቸውን ቁጥር ለመጨመር እንደ ጥሩ አጋጣሚ ተጠቅመውበታል፡፡

- ተከተዩ የነበረው ጆርጅ ስፓርም የነፍስን ዘላለማዊነትና፤ ኃጢአተኞችም የሚጠብቃቸውን ዘላለማዊ ፍርድን በመካድ የሰበከውን ስብከት አሳተመ፡፡

- የክርስቶስንም ዳግም መምጣት ወደ 1914 ዓ.ም. በመቀጠልም ወደ 1933 ዓ.ም. በመጨረሻም ወደ 1995 ዓ.ም. በመቀየር አወጁ፡፡ ግን አንዱም አልሆነም፡፡ የ1995ቱም ግምት የመሲህን መምጣት ከሚጠብቁ ከአይሁድ ረበናት ጋር ተጋጥሞ ነበር፡፡

- አድቬንቲስቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉም በላይ የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ነው ሌላው ሁሉ ከዚህ ቀጥሎ የሚታይ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

- በራእይ 20 ላይ የተጻፈውንም ወስደው በማጣመም በ ሺ የክርስቶስ አገዛዝ ዘመን ጻድቃን ብቻ ይነሱና ከሺው ዓመት በኋላ እንደገና ክርስቶስ ለሦስተኛ ጊዜ ይመጣል ይላሉ፡፡

1. ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች (The 7th Day Adventists)…

- ሦስተኛም ሲመጣ ኃጥአን ይነሱና ሰማያዊው እሳት ወዲያው ያጠፋቸዋል፡፡ ምድርም በጻድቃን ብቻ የምትወረስ አዲስ ትሆናለች በዚህም የዘላለማዊቱ ገነት ኑሮ ይጀመራል ይላሉ፡፡
- በኦርቶዶክሳዊ አተረጓጎም ሺ ዓመት የተባለው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ፤ በመስቀል ተሰቅሎ ሲኦልን መዝብሮ የሰውን ልጅ ነጻ ያወጣበትና በትንሳኤው የሰውን ልጅ ከዲያቢሎስ ተገዢነት ነጻ መሆን ያረጋገጠበት ምሳሌ ሲሆን፤ ይኸም የሚቀጥል መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ቁጥሩም ምልክት ነው፡፡ ከዓለምም መፈጸምም በፊት ዲያቢሎስ ጥቂት ድልን በኃጢአተኞች ላይ ይቀዳጃል፡፡ ግን ለጥቂት ዘመን ነው፡፡ በመቀጠልም አምላካችን ለፍርድ ዳግም ይመጣል፡፡ ነፍስም ከሥጋ ጋር ተዋሕዳ የሰው ዘር ሁሉ ጻድቃንም ኃጥአንም ይነሳሉ፡፡ የዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 20 ትርጉም ይኸው ነው፡፡ በተለይ የዮሐንስ ራዕይ በምሳሌዎችና በምልክቶች የተሞላ ስለሆነ በጥንቃቄ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በተረጎሙ አባቶችና በእግዚአብሔር ገላጭነት መረዳት ያስፈልጋል፡፡
- ጌታችንም ስለ ዳግም ምጽአቱ ያስተማረው ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦ ይገኛል፡፡ ማቴ 24፡1፤ 1ኛ ተሰ 4፡13-18፤ 1ኛ ተሰ 5፡1-3፤ … ይህም አስተምህሮ ጋር በምንም አይገናኝም፡፡ ወንጌላቱም ስለ አምላካችን ሁለቱም ምጽአቶች አንደኛ በቤተልሖም ስለመወለዱና ወደ ዓለም ሥጋ ለብሶ ስለመምጣቱ፤ ሁለተኛም ለዓለም ፍጻሜ ለፍርድ ዳግም ስለመምጣቱ ያስረዳሉ፡፡
- ቅዳሜን ብቻ እንደሰንበት መቁጠርን የመሰሉ የአድቬንቲስቶች አንዳንድ አስተምህሮዎች ስለ ወደፊት አይሁዳዊው መሲህ ይወለዳል ከሚሉ ከአይሁድ ረበናት የተወሰዱ ሲሆኑ ስለሦስተኛም የክርስቶስ ምጽአት የሚያስተምሩት ትምህርት ግን ሙሉ በሙሉ በራሳቸው የተፈጠረ ነው፡፡

2. የይሆዋ ምስክሮች (Jehovah Witness)

- እነዚህ ክርስቲያኖችንንና የክርስቲያን መንግሥታትን የሚቃወሙ ናቸው፡፡ የተመሰረተው በ19ኛው መቶ ክፍለዘመን መጨረሻ በአሜሪካ ሲሆን በ1930 ዓ.ም በርካታ የገንዘብ አቅም በመመደብ እየተስፋፋ ሄደ፡፡ መሥራቹም ቻርለስ ራስል የተባለ አሜሪካዊ ነው፡፡

- ራስል በወጣትነት ዘመኑ በአርዮሳውያንና በአድቬንቲስቶች የኑፋቄ ትምህርት ተጽእኖ ሥር ወደቀ፡፡ የራሱንም አስተምህሮ በመቅረጽ አሳትሞ በሰሜን አሜሪካ አሰራጨ፡፡ እትሙም የዎች ታዎር እትም እየተባለ ይጠራ ጀመር፡፡

- የዎች ታወር የኅትመት ውጤቶች በ27 ቋንቋ የሚታተም ሲሆን በ150 አገሮችም ወኪሎች አሉአቸው፡፡ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ቢጠቀሙም ትምህርታቸው ከክርስተና ትምህርት ጋር ፈጽሞ አይገናኝም፡፡ እንቅስቃሴአቸውም የሃይማኖትና የፖለቲካ ቅልቅል ያለበት ነው፡፡

- አብያተ ክርስቲያናትንም የ#ሰይጣን ተቋማት; ብለው የሚጠሩ ሲሆን የነርሱንም ምስክርነት ስለ እግዚአብሔር ቁጣና እግዚአብሔርም የክርስቲያኖችን አብያተ ክርስቲያናት ለመበቀል እንደ ፈጠራቸው ያስረዳሉ፡፡

- የክርስቲያኖች አብያተ ክርስቲያናትና መንግሥታትም ፈጥነው እንደሚጠፉ ይሰብካሉ፡፡ ፓለቲካንም በተመለከተ የማርክሲስትን ርዕዮተ ዓለም የሚሰብኩ ናቸው፡፡

- ወደ ፊትም ማኅበራዊም ሆነ ሌሎች እኩልነቶችን ለድሃውም ሆነ ለሀብታሙ እንደሚያመጡ፤ ለሁሉም ሥራ እንደሚያቀርቡ፤ ምግብን ለሁሉ እንደሚያዳርሱ፤ የዓለም ጦርነት እንዲያከትም ራሳቸውን ምክንያት አድርገው ቃል ይገባሉ፡፡

2. የይሆዋ ምስክሮች (Jehovah Witness)…

- ዋናው ዓላማቸውና ግባቸው የኣለምን ኃይልና ሥልጣን መቆጣጠር ነው፡፡ አሜሪካንና አንዳንድ መንግሥታትን ሲነቅፉ የለየለት ክህደት ያለባቸውን አገሮችና እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ ግን ፈጽሞ የሚሉት ምንም የለም፡፡

- ተከታዮቻቸው ለተወሰኑ ጉዳዮች ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጠቀሙ፤ ደም እንዳይለግሱ፤ ሀገርን ለመከላከል በሚኖሩ ጉዳዮች ሁሉ ከወገኖቻቸው ጋር ዘብ እንድይቆሙ፤ ዶግማን እንደፈቀዱት እንዲለዋውጡ ይነገራቸዋል፡፡ ይህም አካሄዳቸው ክርስቲያናዊ ትውፊትንና ባህልን እንዲሁም ከየትኞቹም የዓለም መንግሥታት ክርስትናን ሆን ብሎ ለማጥፋት የታለመ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

አሁንም

#*እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን፦ አንሄድባትም አሉ፡፡*;

ኤር. 6፡16፡፡

የይሆዋ ምስክሮች (Jehovah Witness)

የኑፋቄ ትምህርቶቻቸው የትኞቹ ናቸው...

ይቀጥላል...

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡